


# ስለ ልጆች

*ከካህሊል ጂብራን*

ልጆቻችሁ የእናንተ አይደሉም
ሕይወት በራስዋ ምኞት የወለደቻቸው ልጆቿ ናቸው።
በእናንተ ቢመጡም ከእናንተስ አይደሉም፣
አብረዋችሁ ቢኖሩም ገንዘባችሁ እንዳልሆኑ ዕወቁ።
ፍቅራችሁን ብትሰጧቸውም ሓሳባችሁን አትሰጧቸውም፣
የራሳቸው የሆነ ሓሳብ አላቸውና።
አካላቸውን ብታስጠልሉም ለነፍሳቸው ቤት አትሠሩላትም፣
የነርሱ ነፍስ በነገው ቤቷ መኖሪያዋ አላትና፣
እናንተ ፈጽሞ በሕልማችሁም ቢሆን መጎብኘት ከማይቻላችሁ!
እንደነርሱ መሆን ብትጥሩ ደግ፣
እንደናንተ እንዲሆኑ ግን አትድከሙ።
ሕይወት ወደኋላ አትሄድምና፣ ወደ ትላንትም አትመለስም።
እናንተ እንደ ወርዋሪ መንትግ ወይም ቀስት፣
ልጆቻችሁም እንደ ተወርዋሪ ሕያው ፍላጻ ናቸው።
ቀስተኛው ከፊቱ ወዳለው ዘልዓለማዊ መንገድና ዒላማ ያነጣጥራል፤
ባለውም ሙሉ ኃይል ስቦ ሲያጎብጣችሁ
ቀስቶቹ ፈጥነውና ርቀው እንዲወረወሩለት ብሎ ነው።
እንግዲያውስ በቀስተኛው እጅ መወጠርና መጉበጣችን ደስ ይበለን!
በራሪውን ፍላጻ የሚወደውን ያህል
ረጋ ያለውንና የማይናወጸውንም ቀስት ይወዳልና።

ተርጓሚው - ገ/ኢ. ጐርፉ።


